የኢትዮጵያ ፌደራላዊ
ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ለጤና ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

ነባሩ የሥራ ምዘና ሥርዓት ወደ ነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ በመቀየሩ ምክንያት በሥራ ላይ የነበረው የጤና ባለሙያዎች የደረጃ ዕድገትና የተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ ስለተሻረ ለጤና ባለሙያዎች አዲስ የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል።

በዚህ መሠረት ከሚኒስቴሩ ጋር በጋራ ተዘጋጅቶ ከጥር 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል ስምምነት ላይ የተደረሰበትን "በመንግሥት የጤና ተቋማት የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች የቅጥር እና የደረጃ ዕድገት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 3/2013" በማጽደቅ ከዚህ ጋር ተያይዞ መላኩን እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር

ብርሃኑ ፈይሳ ዋላ
ምክትል ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፣</u>

ለክቡር ኮሚሽነር ጽ/ቤት
ለክቡር ም/ኮሚሽነር ጽ/ቤት
ለሰው ሀብት ህጎች ጥናትና ሥርፀት ዳይሬክቶሬት
ለአደረጃጀት፣ ሥራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት
<u>ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን</u>

# ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

# በመንግሥት የጤና ተቋማት የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች የቅጥር እና የደረጃ እድገት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 4/2013

ህዳር 2013ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ

ለረጅም ዓመታት ይሠራበት የነበረውን የሥራ ምደባ ዘዴን በማስቀረት አዲስ የነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴን በመጠቀም በሀገራችን ያሉ የሥራ መደቦች በተመሳሳይ መመዘኛዎች (Factors) ተመዝነው ደረጃ እና ደመወዝ እንዲወስን ለማድረግ በየሴክተር መ/ቤቶች ያሉ የሥራ መደቦች የሥራ ዝርዝር የማዘጋጀት ሥራ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንና በጤና ሚኒስቴር አስተባባሪነት መከናወኑ ይታወሳል፡፡

በዚህ መሠረትም የጤና ሙያ እና የጤና ሥራ አመራር የሥራ መደቦች የሥራ ዝርዝር መግለጫዎች በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ከወረዳ እስከ ፌደራል ጤና ሚኒስቴር ያሉና የተጠሪ ተቋማት የጤና ሥራ አመራር መደቦች ከአንድ እስከ አራት ተዋረድ የዘርፉን ባለሙያዎች፣ አማካሪዎችን እና የሙያ ማህበራት ተወካዮች በማሳተፍ የሥራ ዝርዝር በማዘጋጀት እንዲመዘኑ ተደርጓል፡፡

በሀገራችን የጤና ባለሙያዎች ስልጠና ሞዴል፣ በጤና ዘርፍ አደረጃጀት፣ እንዲሁም በጤና የሰው ሀብት ስምሪትና የሥራ ወሰን መሠረት ለሁሉም የጤና ሙያዎች የትምህርት ዝግጅትን መነሻ በማድረግ ይህ መመሪያ እስከ ወጣበት ቀን ድረስ ለ146 ዋና ዋና የሙያ ስያሜዎችና በ543 ተዋረድ የጤና ሙያ መደቦች የሥራ ዝርዝር በማዘጋጀትና በመመዘን ከደረጃ VI እስከ XXII ባለው ማዕቀፉ ውስጥ ተካተዋል፡፡

በመሆኑም በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ ክፍተት የነበረው የባለሙያዎች ሥራ ዝርዝር አለመኖርን የሚፈታና ለመጀመሪያ ጊዜ በጤና ሙያ ዘርፎች ወጥ የሆነ የሥራ ዝርዝር (Job Discription) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ይህ መመሪያ ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ ክፍል አንድ አጭር ርዕስ፣ ትርጉም፣ የተፈጻሚነት ወሰን እና የጾታ አገላለጽ የያዘ ሲሆን፣ ክፍል ሁለት የቅጥር፣ የእርከን ጭማሪ እና የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ ዝርዝር አፈጻጸም ይዟል፡፡ ክፍል ሶስት ደግሞ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ በመጨረሻም እስካሁን በጤና ሙያ ዘርፎች የተካተቱ የሥራ መደቦች ዝርዝር፣ ደረጃና የተፈላጊ ችሎታ በአባሪነት ተያይዟል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በመንግስት ጤና ተቋማት የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች የቅጥር እና የደረጃ እድገት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 4/2013 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ጤና ሙያ መደብ" ማለት በጤና ሚኒስቴር እውቅና ያለው የጤና ሥልጠና ፕሮግራምን በማጠናቀቅ ወይም ሙያው ለጤናው ዘርፍ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት አግባብ ባለው አካል የሙያ ምዝገባ ማረጋገጫ የተሰጠው እና በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ በጤና ሚኒስቴር የሥራ ዝርዝር የተዘጋጀለት፣ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተመዝኖ ደረጃ የወጣለትና በዓቢይ የሙያ ዘርፍ 10 የተካተተ ሙያ ነው፡፡
2. "በዓቢይ የሙያ ዘርፍ 10 ማለት" ፡ በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝነው ደረጃ የወጣላቸው የሥራ መደቦች በሙያ ዓይነት ተለይተው የሚሰባሰቡበት የአገልግሎት ዓይነት ነው፡፡
3. "ሚኒስቴር እና ሚኒስተር" ማለት እንደ አገባባቸው ቅደሙ-ተከተሉ የጤና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፤
4. "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነው፡፡
5. "አግባብ ያለው አካል" ማለት እንደ አግባብነቱ የጤና ሚኒስቴር እና/ወይም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ማለት ነው፡፡

6. "ሙያ ማሻሻያ" ማለት አንድ ጤና ባለሙያ ከነበረበት የትምህርት ደረጃ ወደ ሚቀጥለው ከፍ ወዳለ የሙያ ደረጃ ለመሸጋገር የተሰጠ ወይም የተወሰደ ከፍ ያለ ትምህርት ደረጃ ነው፡፡

7. "የሙያ ስያሜ" ማለት አንድን የጤና ባለሙያ ከሌላ የጤና ባለሙያ በሙያው፣ በትምህርት ዝግጅቱና በሚሰጠው የጤና አገልግሎት የተለየ መሆኑን ለማሳየት የተሰጠ መጠሪያ ስም ነው፡፡

8. "አስፈፃሚ አካል" ማለት በጤና ሴክተሩ ከፌዴራል እስከ ክልል/የከተማ አስተዳደር ድረስ ባሉ የጤና አደረጃጀቶች የደረጃ እድገት መሰላልና የደመወዝ ስኬል ለመተግበር ወይም ለማስፈፀም ሥራውን በበላይነት የሚመራ አካል ነው፡፡

9. "የዕድገት መሰላል" ማለት አንድ የጤና ባለሙያ ለደረጃ እድገት የተቀመጡ መስፈርቶችን ቃል በቃል በማሟላት ዝቅ ካለ የሥራ ተዋረድ ወደሚቀጥለው ከፍ ያለ የሥራ ተዋረድ የሚሸጋገርበት ለእያንዳንዱ የሙያ ዘርፍ የተዘረጋ የሥራ ተዋረድ ነው፡፡

10. "ታዋቂ ጆርናል" ማለት፡- በዓለም አቀፍ ወይም በሀገር ደረጃ የጤና ምርምር ጽሁፎችን በማሳተም ተቀባይነት ያገኙ የጤና መጽሄት ማለት ነው፡፡

11. "ችግር ፈቺ የምርምር ፅሁፍ" ማለት ባለሙያው በሥራ ላይ ሆኖ በዋና ተመራማሪነት የሚያዘጋጃቸው የጤና ምርምሮች ናቸው፡፡ ሆኖም በትምህርትና ስልጠና ማሟያ የሚሠራን ምርምር አይጨምርም፡፡

12. "የመንግሥት ጤና ተቋም" ማለት በመንግስት የሚተዳደር ወይም የጤና ሙያተኛው በሙያው ተቀጥሮ የሚያገለግልበት መንግስታዊ መሥሪያ ቤት ማለት ነው፡፡

13. "የጤና ጽ/ቤት" ማለት የጤና ተቋም፣ ክልል ጤና ቢሮ፣ የከተማ ጤና ጽ/ቤት፣ የዞንና፣ የወረዳና የቀበሌ ጤና ጽ/ቤት፣ የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር እና ለሚኒስቴሩ ተጠሪ የሆነ ተቋም ነው፡፡

14. "የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ሰርተፊኬት" ማለት አንድ ባለሙያ የጤና አገልግሎት ለመስጠት ሙያዊ ብቃት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ በሰለጠነበት የሙያ መስክ የጤና አገልግሎት መስጠት እንዲችል የሚሰጥ ህጋዊ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

15. "የሥራ ወሰን" ማለት አንድ የጤና ባለሙያ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በፀደቀ የሥራ ዝርዝር መሠረት ለሙያ ዘርፉ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃና ከመነሻ ተዋረድ እስከደረሰበት ተዋረድ የተዘረዘሩ ተግባራትን ያጠቃለለ ነው፡፡

16. "ገምጋሚ አካል" ማለት አንድ ባለሙያ በተመደበበት የሥራ ቦታ ሥራውን በተገቢው ሁኔታ እየተወጣ መሆኑን በማረጋገጥ የባለሙያውን የውጤት ተኮር ምዘና በማካሄድ የሚገመግምና ውጤቱን ለሚመለከተው አካልና ለባለሙያው የሚያሳውቅ የቅርብ ኃላፊ ነው፡፡

17. "የሙያ ስያሜ" ማለት የጤና ባለሙያ ከሌላ የጤና ባለሙያ በሙያው፣ በትምህርት ዝግጅቱና በሰጠው አገልግሎቱ (Junior, Senior, Chief, Expert, Senior Expert, Chief expert, Consulatant) ተብሎ የተሰጠ መጠሪያ ስም ነው፤

3. የተፈፃሚነት ወሰን

መመሪያው በሁሉም የመንግስት ጤና ተቋማት ውስጥ በጤና ሙያ መስክ በሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4. የፆታ አገላለፅ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ዝርዝር አፈጻፀም

### 5. ቅጥር

5.1 አንድ የጤና ባለሙያ መንግሥታዊ ባልሆነ ተቋም አገልግሎ ወደ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ወይም ጤና ተቋም ሲገባ በሰለጠኑበት የጤና ሙያ አገልግሎት ስለመስጠቱና የመንግስት ግብር ስለመክፈሉ ማረጋገጫ ካቀረበ አገልግሎቱ ተይዞ ባለው ክፍት የሥራ መደብ ላይ ሊቀጠር ይችላል፡፡

5.2 በተለያዩ ምክንያቶች ደርሶበት ከነበረው ከፍ ያለ የሥራ ደረጃ ሥራ ባቋረጠ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ዝቅ ብሎ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተቀጠረ የጤና ባለሙያ የሙከራ ቅጥር ጊዜውን እንዳጠናቀቀ ቀድሞ ደርሶበት ወደነበረው ደረጃ ከፍ ተደርጎ ደመወዙ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

### 6 የዕርከን ጭማሪ

6.1 ለመደበኛ የደመወዝ ጭማሪ የተቀመጡ የቆይታ ጊዜ 2 ዓመት እና የውጤት ተኮር ምዘና ውጤቱ መካከለኛ ወይም (65%) እና በላይ የሆነ የጤና ባለሙያ ከኮሚሽኑ በሚወጣ መመሪያ መሠረት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (1) በተቀመጠ ጊዜ ገደብ መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ያገኛል፡፡

6.2 በአንድ የጤና ሙያ መስመር የመጨረሻ ተዋረድ ላይ የደረሰ ለመደበኛ የደመወዝ ጭማሪ የተቀመጡ መስፈርቶችን ሲያሟላ ቆይታውን በመጠበቅ ወደ ጎን እስከ ሥራ ደረጃው የጣሪያ ደመወዝ ድረስ የሁለት ዓመቱ መደበኛ የዕርከን ጭማሪ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

6.3 አንድ የጤና ባለሙያ መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ካገኘ በኋላ ባሉ ሁለት ዓመታት የደረጃ ዕድገት ካገኘ ነባር የጭማሪ ኡደቱ ተቀይሮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሠረት የጭማሪ ኡደቱ ይቀጥራል፡፡

## 7 የጤና ሙያ ሥራ መደቦች የዕድገት መሰላል እና የሚጠየቅ የሥራ ልምድ

7.1 የእያንዳንዱ የጤና ሙያ ሥራ መደብ መጠሪያ ሙያውን የሚገልጽና ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ የደረጃ ተዋረዱን ለማመልከት በየስያሜው መጨረሻ I፣ II፣ III ወይም IV የሚል ቅጥያ ታክሎበታል፡፡

7.2 የጤና ሙያ የሥራ መደቦች ከሁለት እስከ አራት የዕድገት መሰላል እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ከደረጃ III እስከ ደረጃ V ላሉ መለስተኛ ጤና ባለሙያዎች፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪ፣ የህክምና ዶክትሬት ዲግሪና የህክምና ስፔሻሊቲ እያንዳንዳቸው አራት ተዋረድ ሲኖራቸው፣ የሰብ-ስፔሻሊቲ ሶስት ተዋረድ እንዲሁም ሱፐር-ስፔሻሊስት ሁለት ተዋረድ አለው፡፡

7.3 የጤና ሙያ ሥራ መደቦች የዕድገት መሰላል እና በሁሉም ሙያ በየተዋረዱ የሚጠየቅ የቆይታ ጊዜ የሚከተለው ነው፡፡

ሀ. ተዋረድ I........ የሥራ ልምድ አይጠይቅም
ለ. ተዋረድ II...........ሶስት ዓመት የሥራ ልምድ
ሐ. ተዋረድ III.........ስድስት ዓመት የሥራ ልምድ
መ. ተዋረድ IV .......ዘጠኝ ዓመት የሥራ ልምድ

7.4 አንድ የጤና ባለሙያ በፌዴራል ወይም በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ባለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከተቀጠረ ከነበረበት መሥሪያ ቤት የተሞላለትን የውጤት ተኮር የምዘና ውጤት በመጠቀም አገልግሎቱ ለቀጣይ የደረጃ ዕድገት ይያዝለታል፡፡

7.5 ለአንድ የጤና ሙያ ሥራ መደብ የተሰጠ የመደብ መታወቂያ ቁጥር እንደተጠበቀ ሆኖ መጠሪያና ደረጃው ተፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ እንደሚመደብበት የጤና ባለሙያ የሚቀያየር ይሆናል፡፡

7.6 በሙያ ማሻሻያ የተገኘ እያንዳንዱ የጤና ሙያ አንዱ ከሌላው ተለይቶ የራሱ ተዋረድ እንዲኖረው ስለተደረገ ለተሻሻለው አዲስ ሙያ ከነባሩ የሚተላለፍ አገልግሎት አይኖረውም፡፡

## 8 የሥራ ወሰን

8.1 አንድ የጤና ባለሙያ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በፀደቀው የሥራ ዝርዝር መሠረት ለሙያ ዘርፉ ከዝቅተኛ እስከ ደረሰበት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃና ከመነሻ ተዋረድ እስከደረሰበት የሥራ ተዋረድ የሥራ ወሰን የተዘረዘሩ ተግባራትን የመሥራት መብትና ግዴታ አለበት። (ለአብነት አንድ ተዋረድ III ላይ የደረሰ የጠቅላላ ሀኪም፣ የስፔሻሊቲ እና የሰብ-ስፔሻሊቲ ሁሉም ተዋረዶች ተግባራት ወይም ሥራ ወሰን ያከናውናል)።

8.2 አሠሪው ተቋም ለሙያ ዘርፉ የተቀመጠውን የሥራ ወሰን ተግባራት በተናጠል ወይም በማዋሃድ እንደአስፈላጊነቱ የማሠራት መብት አለው።

## 9 የትምህርት ማሻሻያ

9.1 በተቋም ወጪ የሙያ ማሻሻያ የትምህርት ዕድል የሚሰጠው የጤና ባለሙያ ትምህርቱን አጠናቅቆ ሲመለስ በሰለጠነበት ሙያ ሊመደብበት የሚችል ተመዝና ደረጃ የወጣለት የጤና ሙያ የሥራ መደብ መኖሩን በቅድሚያ ተቋሙ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

9.2 በተቋሙ ፍላጎት አንድ የጤና ባለሙያ ሙያውን አሻሽሎ ሲመለስ ቢያንስ ለትምህርት ከመሄዱ በፊት ደርሶበት ከነበረው ደረጃ በታች አይመደብም። በዚህ መሠረት የትምህርት ደረጃ ያሻሻለ የጤና ባለሙያ፡-

ሀ) በሰለጠነበት የሙያ መስመር የትምህርት ደረጃውን አሻሽሎ ሲመለስ ለትምህርት ከመሄዱ በፊት ደርሶበት የነበረው ደረጃ ዝቅ ያለ ከሆነ በሰለጠነበት ሙያ የመጀመሪያ ተዋረድ ወይም ዕድገት መሰላል ላይ ተመድቦ ለደረጃው የተወሰነው ደመወዝ ይከፈለዋል።

ለ) በሰለጠነበት የሙያ መስመር ትምህርት ደረጃውን አሻሽሎ ሲመለስ ለትምህርት ከመሄዱ በፊት ደርሶበት ከነበረው ደረጃ እኩል ወይም በላይ ከሆነ የሚከፈለውን ደመወዝ እንደያዘ በአዲሱ ሙያው በትያዩ ባለ አቻ ደረጃ ላይ ይመደባል።

9.3 የትምህርት ማሻሻያ ያደረገ የጤና ባለሙያ ባሻሻለው የትምህርት ደረጃ ተመድቦ ሥራ የጀመረበት ቀን መነሻ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሠረት የሥራ ልምዱ ለመደበኛ የደመወዝ ጭማሪ እና ለደረጃ ዕድገት ይያዝለታል፡፡

9.4 በአሠሪው ተቋም የተሰጠውን የትምህርት እድል በተለያዩ ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች አቋርጦ የተመለሰ የጤና ባለሙያ ለትምህርት ከመሄዱ በፊት ይዞት በነበረው የሥራ መደብ ላይ ያገለገለበት ጊዜ ለቀጣይ የደረጃ ዕድገት ይያዝለታል፡፡

9.5 አንድ የጤና ባለሙያ በመደበኛ ሥራ ሰዓት ትምህርት ላይ ያሳለፈው ጊዜ እንደሥራ ልምድ አይያዝም፡፡

## 10 መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ እና የደረጃ እድገት የሚሰጥበት ወቅትና ዝርዝር አፈፃፀም

10.1 መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ወይም የደረጃ ዕድገት የሚሰጠው በዓመት ውስጥ በሐምሌ ወይም በጥር ወር መጀመሪያ ሆኖ፡-

ሀ) ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ታሕሣሥ 30 ቀን የተቀጠረ ወይም በሙያ ማሻሻያ የደረጃ ለውጥ ያደረገ ከጥር 1 ጀምሮ፤

ለ) ከጥር 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን የተቀጠረ ወይም በሙያ ማሻሻያ የደረጃ ለውጥ ያደረገ ከሐምሌ 1 ጀምሮ፤

መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ወይም የደረጃ ዕድገት ይሰጠዋል፡፡

10.2 የጤና ባለሙያዎች የደረጃ ዕድገት እንደሁኔታው በመንግስት የጤና ተቋም በሚቋቋም ኮሚቴ ወይም ይህንኑ ተግባር እንዲያስፈጽም በሚሰየም ኮሚቴ ወይም አነስተኛ የጤና ባለሙያዎች ቁጥር ባሉበት ተቋም በሰው ሀብት አስተዳደር የሥራ ዘርፍ አማካይነት ይከናወናል፡፡

## 11 የደረጃ ዕድገት መስፈርቶች

ማንኛውም የጤና ባለሙያ ለደረጃ ዕድገት ብቁ ለመሆን ለመደቡ የተቀመጡ መስፈርቶችን ቃል በቃል ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡ ዋና ዋናዎቹ የደረጃ ዕድገት መስፈርቶች፡-

11.1 የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10.1 እንደተጠበቀ ሆኖ ሶስት ዓመት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ሳይቋረጥ የተሰጠ አገልግሎት፣

11.2 ከደረጃ ዕድገት መስጫ ወቅት በፊት ያሉ የመጨረሻ አራት ተከታታይ አማካይ የውጤት ተኮር ምዘና ውጤት መካከለኛ ወይም 65% እና በላይ ያስመዘገበ፣

11.3 ከደረጃ I እስከ ደረጃ V የትምህርት ዝግጅት ለሚጠይቁ ሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና

11.4 የታደሰ የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ምስክር ወረቀት፣

ናቸው።

11.5 በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 11.1-11.4 የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት እና በላይ ደረጃ የደረሰ የጤና ባለሙያ በሙያ መስኩ ችግር ፈቺ ምርምር በመሥራት ውጤቱን በታዋቂ ጆርናል ማሳተሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ በሚኒስቴሩ ተቀባይነት ካገኘ፣ ለቀጣይ የሥራ ደረጃ የሚጠበቅበትን የሶስት ዓመት ቆይታ በአንድ ዓመት ይቀንስለታል።

11.6 ችግር ፈች የምርምር ጽሁፍ ለደረጃ ዕድገት የሚያዘው በግሉ በዋና ተመራማሪነት (Lead researcher) ለሠራ የጤና ባለሙያ ብቻ ነው።

## 12 የጤና ሥራ አመራር የሥራ መደቦች ላይ የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ

የጤና ሥራ አመራር የሥራ መደቦች ልዩ ባህርይ ምክንያት እንደሁኔታው የደረጃ ዕድገት ተጠቃሚ የሆኑ የጤና ባለሙያዎች ወይም ሌሎች ሙያተኞች ሊመደቡ ይችላሉ። የሥራ መደቦቹ ተዋረድ ቢኖራቸውም የደረጃ ዕድገት የሚሰጥባቸው ስላልሆኑ አመዳደቡ እንደሚከተለው ይሆናል፦

12.1 አግባብ ባለው የጤና ሙያ ትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ ያለው የጤና ሙያተኛ ለአንዱ የጤና ሥራ አመራር መደብ የተቀመጠው የሥራ ልምድ መጠን ባይኖረውም ኃላፊነቱን በብቃት ሊወጣ ይችላል ብሎ ተቋሙ ካመነበት የደረሰበትን የሙያ ስያሜ፣ ደረጃ እና ደመወዝ እንደያዘ ያለውድድር በጤና ሥራ አመራር መደብ ላይ ሊመደብ ይችላል።

ይዝ የማህ አመንን
የተሀማህ አደኖሥራ ምነ
የሰው ሃ/ል/ዳይሬክቶሬት

12.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12.1 መሠረት የተመደበ የጤና ባለሙያ በጤና ሥራ አመራር መደብ ላይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ ለቀጣይ የኬርየር ዕድገት ይያዝለታል፡፡

12.3 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12.1 እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ በጤና ሥራ አመራር መደብ ላይ ለሥራ መደቡ የተቀመጠውን የተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ ቃል በቃል የሚያሟላን የጤና ባለሙያ ወይም የጤና ባለሙያ ያልሆነ ሠራተኛ አወዳድሮ መመደብ ይችላል፡፡

12.4 በጤና የሥራ አመራር የሥራ መደብ ላይ ሆኖ በጤና ሙያው የደረጃ ዕድገት እያገኘ ያገለገለ የጤና ባለሙያ በሙያው የመጨረሻ የዕድገት መሰላል ላይ ከደረሰ እና የተመደበበት የጤና የሥራ አመራር መደብ የሥራ ደረጃ ከደረሰበት የሥራ ደረጃ ከፍ ያለ ከሆነ የሥራ አመራር መደቡ የሚያስገኘውን ጥቅም ማግኘት የሚችለው ለመደቡ የተቀመጠውን የሥራ ልምድ አሟልቶ ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ተወዳድሮ ከተመረጠ ብቻ ይሆናል፡፡

## 13 የደረጃ ዕድገት የማይሰጥባቸው ሁኔታዎች

13.1 በከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ምክንያት በጊዜ ገደብ ከደረጃና ከደመወዝ ዝቅ እንዲል የተወሰነበት፣

13.2 በደረጃ ዕድገት መስጫ ወቅት የደረጃ ዕድገቱ የታገደበት፣

13.3 ለጡረታ በሕግ ከተወሰነው የዕድሜ ጣሪያ ለመድረስ ሦስት ወራት እና ያነሰ ጊዜ የሚቀረው፣

13.4 ለአንድ ዓመት እና በላይ ለሙያ ማሻሻያ ስልጠና ወይም ለመደበኛ ትምህርት ተልኮ በመከታተል ላይ ያለ፣

የጤና ባለሙያ የደረጃ ዕድገት አያገኝም፡፡

# ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14 ጊዜያዊ የመሸጋገሪያ የሥራ መደቦች

14.1 ሐምሌ 16 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ፐ/ለ/ሚ30/ጠ10/91/172 በወጣው የጤና ባለሙያዎች የድልድል አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (1) ከጤና ትምህርት የሥልጠና ፕሮግራም ውጭ ከተደረጉ የሰርተፊኬት ደረጃ የቀድሞ ጤና ሙያ መደቦች መካከል በሥራ ላይ ያሉ ሙያተኞች ሙያቸውን እስከሚያሻሽሉ ድረስ ብቻ እንዲመደቡባቸው ለጤና ረዳት፣ ለመሰስተኛ ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ፣ ለረዳት ነርስ፣ ለመለስተኛ ላቦራቶሪ ቴክኒሽያን፣ ለረዳት ፋርማሲ ቴክኒሽያን እና ለራዲዮሽን ቴራፒስት (RTT)፣ ጊዚያዊ የሥራ ዝርዝር መግለጫ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ያሉ ነባር ሙያተኞች ብቻ እንዲመደቡባቸው ተደርጓል።

14.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (14.1) ዝርዝራቸው በተመለከተ ጊዜያዊ የሥራ መደቦች ላይ የአዲስ ሠራተኛ ቅጥር መፈፀም አይቻልም።

### 15 የመሸጋገሪያ መመሪያ

የነጥብ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት የደመወዝ ስኬል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2012 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ከነባር የምዘና ሥርዓት በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ወደተመዘኑ ደረጃዎች በተደረገ ሽግግር ያገኙት የመሸጋገሪያ ጭማሪ መጠን በሶስት ዙር ከተከፈላቸው የጤና ሙያተኞች መካከል በጥር 2013 ዓ.ም የሚያገኙት የደረጃ እድገት ህዳር 2 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር ሲ/ሲ/ክ30/ጠ10/92/185 በተላለፈው መመሪያ መሠረት ይፈጸማል።

### 16 የተያያዙ አባሪዎች ህጋዊነት

16.1 ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዙ አባሪዎች የዚህ መመሪያ አካል ናቸው።

Civil Service Commission

16.2 ለወደፊቱ ከነጥብ የሥራ ምዘና ጋር በኮሚሽኑ ጸድቀው የሚወጡ የጤና ባለሙያዎች ደረጃና ተዋረድ የዚህ መመሪያ አካል ይሆናሉ፡፡

17 የተሻሩ መመሪያዎች

17.1 በ1992 የወጣው እና በ1994 ዓ.ም የተሻሻለው የጤና ባለሙያዎች የደረጃ ዕድገት መሰላል የአፈፃፀም መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

17.2 ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

18 መመሪያውን ስለማሻሻል

18.1 ሚኒስቴሩ በዝርዝሩ ያልተካተቱ የሙያ ዘርፎችን አስፈላጊነት በማጥናት አግባብ ባለው አካል ተመዝነው ደረጃ እንዲወጣላቸው ከተደረገ በኋላ ለአስፈፃሚ አካላት በየጊዜው የሚያሳውቅ ይሆናል፡፡

18.2 በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እየቀረበ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

19 ተጠያቂነት

የዚህ መመሪያን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ቅጥር፣ መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ደረጃ ዕድገት የሚፈጽም የሥራ ኃላፊ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

20 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥር 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጤና ሚኒስቴር

# በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ የተመዘኑ

# የ146 ዋና ዋና የሙያ ስያሜ 543 ተዋረድ የጤና ሙያ መደቦች

## ከ2010 እስከ 2013 ዓ.ም

*ታህሳስ 2013 ዓ.ም*

*አዲስ አበባ*

| ሙያ ዘርፍ | ተዋረድ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | የሥራ ልምድ በዓመት |
|---|---|---|---|---|
| 7 | 25 | ደረጃ 3 ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ I | IX | 0 |
| | 26 | ደረጃ 3 ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ II | X | 3 |
| | 27 | ደረጃ 3 ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ III | XI | 6 |
| | 28 | ደረጃ 3 ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ IV | XII | 9 |
| | | | | |
| 8 | 29 | ህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ (HO) I | XII | 0 |
| | 30 | ህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ (HO) II | XIII | 3 |
| | 31 | ህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ (HO) III | XIV | 6 |
| | 32 | ህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ (HO) IV | XV | 9 |
| | | | | |
| 9 | 33 | ፐብሊክ ሄልዝ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIII | 0 |
| | 34 | ፐብሊክ ሄልዝ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XIV | 3 |
| | 35 | ፐብሊክ ሄልዝ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XV | 6 |
| | 36 | ፐብሊክ ሄልዝ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVI | 9 |
| | | | | |
| 10 | 37 | ፐብሊክ ሄልዝ ስፔሻሊስት I | XV | 0 |
| | 38 | ፐብሊክ ሄልዝ ስፔሻሊስት II | XVI | 3 |
| | 39 | ፐብሊክ ሄልዝ ስፔሻሊስት III | XVII | 6 |
| | 40 | ፐብሊክ ሄልዝ ስፔሻሊስት IV | XVIII | 9 |
| | | | | |
| 11 | 41 | ድንገተኛና ጽኑ ሕሙማን እንክብካቤ ነርስ ፕሮፌሽናል I | XI | 0 |
| | 42 | ድንገተኛና ጽኑ ሕሙማን እንክብካቤ ነርስ ፕሮፌሽናል II | XII | 3 |
| | 43 | ድንገተኛና ጽኑ ሕሙማን እንክብካቤ ነርስ ፕሮፌሽናል III | XIII | 6 |
| | 44 | ድንገተኛና ጽኑ ሕሙማን እንክብካቤ ነርስ ፕሮፌሽናል IV | XIV | 9 |
| | | | | |

| ሙያ ዘርፍ | ተዋረድ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | የሥራ ልምድ በዓመት |
|---|---|---|---|---|
| | 70 | አንስቴዥዮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XIV | 3 |
| | 71 | አንስቴዥዮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XV | 6 |
| | 72 | አንስቴዥዮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVI | 9 |
| | | | | |
| 19 | 73 | ደረጃ 4 ነርስ I | IX | 0 |
| | 74 | ደረጃ 4 ነርስ II | X | 3 |
| | 75 | ደረጃ 4 ነርስ III | XI | 6 |
| | 76 | ደረጃ 4 ነርስ IV | XII | 9 |
| | | | | |
| 20 | 77 | ነርስ ፕሮፌሽናል I | XI | 0 |
| | 78 | ነርስ ፕሮፌሽናል II | XII | 3 |
| | 79 | ነርስ ፕሮፌሽናል III | XIII | 6 |
| | 80 | ነርስ ፕሮፌሽናል IV | XIV | 9 |
| | | | | |
| 21 | 81 | ቀዶ ህክምና ነርስ ፕሮፌሽናል I | XI | 0 |
| | 82 | ቀዶ ህክምና ነርስ ፕሮፌሽናል II | XII | 3 |
| | 83 | ቀዶ ህክምና ነርስ ፕሮፌሽናል III | XIII | 6 |
| | 84 | ቀዶ ህክምና ነርስ ፕሮፌሽናል IV | XIV | 9 |
| | | | | |
| 22 | 85 | ቀዶ ህክምና ክፍል ነርስ ፕሮፌሽናል I | XI | 0 |
| | 86 | ቀዶ ህክምና ክፍል ነርስ ፕሮፌሽናል II | XII | 3 |
| | 87 | ቀዶ ህክምና ክፍል ነርስ ፕሮፌሽናል III | XIII | 6 |
| | 88 | ቀዶ ህክምና ክፍል ነርስ ፕሮፌሽናል IV | XIV | 9 |
| | | | | |
| 23 | 89 | ጨቅላ ህፃናት ነርስ ፕሮፌሽናል I | XI | 0 |
| | 90 | ጨቅላ ህፃናት ነርስ ፕሮፌሽናል II | XII | 3 |
| | 91 | ጨቅላ ህፃናት ነርስ ፕሮፌሽናል III | XIII | 6 |
| | 92 | ጨቅላ ህፃናት ነርስ ፕሮፌሽናል IV | XIV | 9 |
| | | | | |
| 24 | 93 | ህፃናትና ታዳጊዎች ነርስ ፕሮፌሽናል I | XI | 0 |

Democratic Republic of Ethiopia
Civil Service Commission

| ሙያ ዘርፍ | ተዋረድ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | የሥራ ልምድ በዓመት |
|---|---|---|---|---|
| 93 | 355 | ራዲዮሎጂ ስፔሻሊስት I | XVI | 0 |
| | 356 | ራዲዮሎጂ ስፔሻሊስት II | XVII | 3 |
| | 357 | ራዲዮሎጂ ስፔሻሊስት III | XVIII | 6 |
| | 358 | ራዲዮሎጂ ስፔሻሊስት IV | XIX | 9 |
| | | | | |
| 94 | 359 | ራዲዮሎጂ ሰብ-ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 360 | ራዲዮሎጂ ሰብ-ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 361 | ራዲዮሎጂ ሰብ-ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |
| | | | | |
| 95 | 362 | ጋስትሮ ኢንተሮሎጂና ሄፓቶሎጂ ሰብ-ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 363 | ጋስትሮ ኢንተሮሎጂና ሄፓቶሎጂ ሰብ-ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 364 | ጋስትሮ ኢንተሮሎጂና ሄፓቶሎጂ ሰብ-ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |
| | | | | |
| 96 | 365 | ዩሮሎጂ ቀዶ ህክምና ስፔሻሊስት I | XVI | 0 |
| | 366 | ዩሮሎጂ ቀዶ ህክምና ስፔሻሊስት II | XVII | 3 |
| | 367 | ዩሮሎጂ ቀዶ ህክምና ስፔሻሊስት III | XVIII | 6 |
| | 368 | ዩሮሎጂ ቀዶ ህክምና ስፔሻሊስት IV | XIX | 9 |
| | | | | |
| 97 | 369 | ፐልሞናሪ እና ክሪቲካል ኬር ሰብ-ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 370 | ፐልሞናሪ እና ክሪቲካል ኬር ሰብ-ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 371 | ፐልሞናሪ እና ክሪቲካል ኬር ሰብ-ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |
| | | | | |
| 98 | 372 | ውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት I | XVI | 0 |
| | 373 | ውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት II | XVII | 3 |
| | 374 | ውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት III | XVIII | 6 |
| | 375 | ውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት IV | XIX | 9 |
| | | | | |
| 99 | 376 | ልብ ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 377 | ልብ ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 378 | ልብ ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |

| መ-ያ ዘርፍ | ተዋረድ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | የሥራ ልምድ በዓመት |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| 107 | 403 | ቤተሰብ ሕክምና ስፔሻሊስት I | XVI | 0 |
| | 404 | ቤተሰብ ሕክምና ስፔሻሊስት II | XVII | 3 |
| | 405 | ቤተሰብ ሕክምና ስፔሻሊስት III | XVIII | 6 |
| | 406 | ቤተሰብ ሕክምና ስፔሻሊስት IV | XIX | 9 |
| | | | | |
| 108 | 407 | ህጻናት ድንገተኛ እና ጽኑ ህክምና ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 408 | ህጻናት ድንገተኛ እና ጽኑ ህክምና ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 409 | ህጻናት ድንገተኛ እና ጽኑ ህክምና ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |
| | | | | |
| 109 | 410 | አዕምሮ ህክምና ስፔሻሊስት I | XVI | 0 |
| | 411 | አዕምሮ ህክምና ስፔሻሊስት II | XVII | 3 |
| | 412 | አዕምሮ ህክምና ስፔሻሊስት III | XVIII | 6 |
| | 413 | አዕምሮ ህክምና ስፔሻሊስት IV | XIX | 9 |
| | | | | |
| 110 | 414 | ኒውሮሳይካትሪ ሰብ-ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 415 | ኒውሮሳይካትሪ ሰብ-ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 416 | ኒውሮሳይካትሪ ሰብ-ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |
| | | | | |
| 111 | 417 | ህጻናትና ወጣቶች አእምሮ ሰብ-ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 418 | ህጻናትና ወጣቶች አእምሮ ሰብ-ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 419 | ህጻናትና ወጣቶች አእምሮ ሰብ-ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |
| | | | | |
| 112 | 420 | አዲክሽን ሳይኪያትሪ ሰብ ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 421 | አዲክሽን ሳይኪያትሪ ሰብ ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 422 | አዲክሽን ሳይኪያትሪ ሰብ ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |
| | | | | |
| 113 | 423 | አረጋውያን አእምሮ ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 424 | አረጋውያን አእምሮ ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 425 | አረጋውያን አእምሮ ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |

| ሙያ ዘርፍ | ተዋረድ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | የሥራ ልምድ በዓመት |
|---|---|---|---|---|
| | 496 | ሜዲካል ባዮቴክኖሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XV | 6 |
| | 497 | ሜዲካል ባዮቴክኖሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVI | 9 |
| | | | | |
| 135 | 498 | ስፒችና ላንጉጅ ቴራፒ ፕሮፌሽናል I | XI | 0 |
| | 499 | ስፒችና ላንጉጅ ቴራፒ ፕሮፌሽናል II | XII | 3 |
| | 500 | ስፒችና ላንጉጅ ቴራፒ ፕሮፌሽናል III | XIII | 6 |
| | 501 | ስፒችና ላንጉጅ ቴራፒ ፕሮፌሽናል IV | XIV | 9 |
| | | | | |
| 136 | 502 | ክሊኒካል ኬሚስትሪ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIII | 0 |
| | 503 | ክሊኒካል ኬሚስትሪ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XIV | 3 |
| | 504 | ክሊኒካል ኬሚስትሪ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XV | 6 |
| | 505 | ክሊኒካል ኬሚስትሪ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVI | 9 |
| | | | | |
| 137 | 506 | ክሊኒካል-ሞለኪዩላር ባዮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIII | 0 |
| | 507 | ክሊኒካል-ሞለኪዩላር ባዮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XIV | 3 |
| | 508 | ክሊኒካል-ሞለኪዩላር ባዮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XV | 6 |
| | 509 | ክሊኒካል-ሞለኪዩላር ባዮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVI | 9 |
| | | | | |
| 138 | 510 | የህጻናት ነርሽ ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት I | XIX | 0 |
| | 511 | የህጻናት ነርሽ ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት II | XX | 3 |
| | 512 | የህጻናት ነርሽ ህክምና ሰብ-ስፔሻሊስት III | XXI | 6 |
| | | | | |
| 139 | 513 | ራድዮ ፋርማሲ (ኑዩክሌር ፋርማሲ) ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIV | 0 |
| | 514 | ራድዮ ፋርማሲ (ኑዩክሌር ፋርማሲ) ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XV | 3 |
| | 515 | ራድዮ ፋርማሲ (ኑዩክሌር ፋርማሲ) ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XVI | 6 |
| | 516 | ራድዮ ፋርማሲ (ኑዩክሌር ፋርማሲ) ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVII | 9 |
| | | | | |
| 140 | 517 | ክሊኒካል ፋርማሲ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIV | 0 |
| | 518 | ክሊኒካል ፋርማሲ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XV | 3 |
| | 519 | ክሊኒካል ፋርማሲ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XVI | 6 |

| መ.ያ ዘርፍ | ተዋረድ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | የሥራ ልምድ በዓመት |
|---|---|---|---|---|
| | 520 | ክሊኒካል ፋርማሲ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVII | 9 |
| | | | | |
| 141 | 521 | ፋርማሲዩቲካል ስፕላይ ቼይን ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIV | 0 |
| | 522 | ፋርማሲዩቲካል ስፕላይ ቼይን ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XV | 3 |
| | 523 | ፋርማሲዩቲካል ስፕላይ ቼይን ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XVI | 6 |
| | 524 | ፋርማሲዩቲካል ስፕላይ ቼይን ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVII | 9 |
| | | | | |
| 142 | 525 | ፋርማኮ ኢፒደሚዮሎጂ እና ሶሻል ፋርማሲ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIV | 0 |
| | 526 | ፋርማኮ ኢፒደሚዮሎጂ እና ሶሻል ፋርማሲ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XV | 3 |
| | 527 | ፋርማኮ ኢፒደሚዮሎጂ እና ሶሻል ፋርማሲ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XVI | 6 |
| | 528 | ፋርማኮ ኢፒደሚዮሎጂ እና ሶሻል ፋርማሲ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVII | 9 |
| | | | | |
| 143 | 529 | ፋርማኮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIV | 0 |
| | 530 | ፋርማኮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XV | 3 |
| | 531 | ፋርማኮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XVI | 6 |
| | 532 | ፋርማኮሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVII | 9 |
| | | | | |
| 144 | 533 | ትሮፒካል ዴርማቶሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XIV | 3 |
| | 534 | ትሮፒካል ዴርማቶሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XV | 6 |
| | 535 | ትሮፒካል ዴርማቶሎጂ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVI | 9 |
| | | | | |
| 145 | 536 | ኒዮናታል ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIII | 0 |
| | 537 | ኒዮናታል ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት II | XIV | 3 |
| | 538 | ኒዮናታል ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት III | XV | 6 |
| | 539 | ኒዮናታል ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት IV | XVI | 9 |
| | | | | |
| 146 | 540 | ሂስቶ ቴክኖሎጂስት I | XI | 0 |
| | 541 | ሂስቶ ቴክኖሎጂስት II | XII | 3 |
| | 542 | ሂስቶ ቴክኖሎጂስት III | XIII | 6 |
| | 543 | ሂስቶ ቴክኖሎጂስት IV | XIV | 9 |

| ሙያ ዘርፍ | ተዋረድ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | የሥራ ልምድ በዓመት |
|---|---|---|---|---|
| | | **ጊዜያዊ የመሸጋገሪያ የሥራ መደቦች** | | |
| | 1 | ጤና ረዳት | X | ሥራ ላይ ላሉ ብቻ |
| | 2 | ራዲዮሽን ቴራፒስት(RTT) | X | ሥራ ላይ ላሉ ብቻ |
| | 3 | መለስተኛ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ | X | ሥራ ላይ ላሉ ብቻ |
| | 4 | አሲስታንት ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኒሽያን | X | ሥራ ላይ ላሉ ብቻ |
| | 5 | አሲስታንት ነርስ | X | ሥራ ላይ ላሉ ብቻ |
| | 6 | አሲስታንት ፋርማሲ ቴክኒሽያን | X | ሥራ ላይ ላሉ ብቻ |